# ለለውጥ መነሳሳት በኢትዮጵያ

አምባገነናዊ ሥርዓት ከስረ-መሰረቱ አስወግዶ በምትኩ ፍትህ የሰፈነበት፣ ዴሞክራሲያዊ መብት የተከበረበትና የህግ የበላይነት የተረጋገጠበትን ሥርዓት ለመገንባት እንዲሁም የሕዝቦቿ ታሪካዊ አነድነትና የግዛቷን ሉዐላዊነት እንዲከበር በየፊናው የሚደረገውን ትግል የሚያግዝ የውይይት መድረክ።

ከሰሜን አፍሪካና ከመካከለኛው ምስራቅ ዴሞክራሲያዊ የለውጥ ማዕበል ምን እንማራለን? በአገራችን ለለውጥ መነሳሳት መንስኤ የሚሆኑ ምክንያቶችን በየደረጃው ተንትኖ በማየት በኤኮኖሚ፣ በሶሻል፣ በሰብአዊ መብት አያያዝ እንዲሁም በፖለቲካ ምህዳር ዙሪያ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ይዳስሳል። ኢትዮጵያ ከሌሎች አገሮች ባልተናነሰ ሁኔታ በውስብስብ ችግሮች የተወጠረች አገር እንደመሆኗ ይህን ለመለወጥ በቅርቡ ውጤት እያስመዘገቡ ከሚገኙ ሕዝባዊ ድሎች ተቋዳሽ ለማረግ ምን መደረግ አለበት በሚለው ንዑድ አሳብ ዙሪያ ስብሰባው በጥልቀት ይመረምራል። የፖለቲካ ድርጅተችና የሲቪክ ተቋማት ያለፉበትን የትግል ጉዞ ድክመትና ጥንካሬ በመጠኑ ገምግሞ ለወደፊቱ ሊተባበሩ በሚችሉባቸው የጋራ መሰባሰቢያ አጀንዳዎች ዙሪያ ህብረት እንዲፈጥሩና ሃይላቸውን በማስተባብረው የአምባገነኖችን ዕድሜ እንዲያሳጥሩ ብሎም ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሽግግር ጥንስሱን እንዲጥሉ ሊያከናውኑ ስለሚገባቸው ተግባሮች መድረኩ ይጠቁማል። ለመጨረሻ ኢትዮጵያዊያን በተለይም በውጭ ነዋሪ የሆነው ሕብረተሰብ በቡድንም ሆነ በነፍስወከፍ ሊያበረክት ስለሚችለው አስተዋጽዖ ይሄው መድረክ በጥሞና ይመለከታል።

ይህ የመወያያ መድረክ ከወትሮው ለየት ባለ ቅንብር ተሳታፊዎች ቁምነገር ገብይተው፣ ረክተውና ተነቃቅተው እንዲሄዱ ለማድረግ በሁሉም መስክ ዕውቀትና ተመክሮ ያካበቱ የድርጅት መሪዎች አገር በቀል ምሁራንና እንዲሁም በአለም አቀፍ የጥናትና ምርምር ተቋማት የተሰማሩ ለኢትዮጵያ በጎ አመለካከት ያላቸውን የውጭ አገር ሞያተኞች፣ እንዲሁም ለአገራችን በሁሉም መስክ በግንባር ቀደምነት አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ግለሰቦችን አሰባጥሮ በተጋባዥነት ይዞ የሚያቀርብ ሲሆን አገር ወድዶች በሥፍራዉ ተገኝታችሁ የውይይቱ ተካፋይ ትሆኑ ዘንድ አዘጋጁ ማርች ፎረ ፍሪደም በትህትና ይጋብዛል።

ቀኑ፡ Sunday June 12, 2011

ቦታው፡ Washington Merriott
**1221 22nd Street NW**
**Washington, DC 20037**

ሰዐት፡ ከ12፡30 ፒ.ኤም ጀምሮ

ስለዝግጅቱ የበለጠ መረጃ ለማግኘት በስልክ ቁጥር (202-686-8070) ወይም
www.march4fredom.org የተሰኘውን ድረ-ገጻችንን ይጎብኙ።